# የፖለቲካ አመራር ትልቁ ሃላፊነት…

ከሃብሮማይ
ghabrom@yahoo.com

አሜሪካዊ የፖለቲካ ተንታኝና እ.ኤ.አ በ 1996 ና በ 2000 ግሪን ፓርቲን ወክሎ፣ በ 2004 ና በ 2008 ደግሞ በግል የአሜሪካ ፕረዚዴንት ለመሆን ተወዳድሮ የነበረ ራልፍ ናደር በፃፈው መፅሐፍ "the future of leadership is to produce more leaders not more followers" ብሏል፡፡ የአመራር ትልቁ ሃላፊነት ብዙ ተተኪ አመራሮችን መፍጠር እንጂ ብዙ ደጋፊዎችን መፍጠር አይደለም" እንደማለት ነው፡፡

አንድ መሪ፣ ብቃት ያለው መሪ የሚባለው ለአመራር ብቃት ያላቸውን ተተኪዎች ሲያፈራ እንደሆነ ብዙ ፀሐፊዎች ይስማማሉ፡፡ ይህን የማብቃት ስራ ለመስራት መደረግ ያለበት ነገር ምንድነው ሲባል፣ በመጀመርያ የተማሩ ወጣቶችና ሴቶች በብዛት ወደ ፓርቲ ማስገባት የግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም አባላትን ሳታፈራ ብቃት ያላቸውን አመራሮችን ማፍራት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ አባላት በአንድ ፓርቲ ውስጥ አባል ስለሆኑ ብቻ ተተኪ አመራሮች ይሆናሉ ማለት አይደለም፡፡አባላትን በተለያዩ የድርጅቱ ስልጠናዎች ማብቃት ይጠይቃል፡፡ እነዚህ አባላት ለመማር ዝግጁነት ያላቸውና በብቃት ተፈትሸው መወጣት የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ውጤታማ ተተኪ አመራሮችን ለማፍራት አባላቱ የገቡበትን ድርጅት ፖሊሲና ስትራተጂ ከመጀመርያም ተረድተውትና አምነውበት መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ አባላቱ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ድርጅቱን ከተቀላቀሉ በማንኛውም ሁኔታ ለፖሊሲውና ስትራተጂው ተገዢና በሚሰሩት የስራ መስክ ላይ ፖሊሲውን ለመፈፀምና ለማስፈፀም ግንባር ቀደም ይሆናሉ፡፡

Board game about principles of democracy and politics የሚል ርዕስ ያለውና በኦርላንዶ ዲ..ጋርሽያ የተፃፈ መፅሐፍ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንደ ፓርቲ ጠንክሮ መስራት የሚችለው አባላትን በብዛትና በጥራት በማፍራት መሆኑን ይጠቁማል፡፡

አንድ ፓርቲ ተቋሙ ጠንካራ ነው ተብሎ የሚፈረጀው ያሉትን አባላት ለተለያዩ የአመራር እርከኖች የሚያበቃ ሲሆን ነው፡፡ ከዚያም አልፎ የጠቅላላ ፓርቲ መሪ መውጣት ያለበት ከአባሎች መሆን ይኖርበታል፡፡ ብዙ አባሎች ማፍራት ብቻ ግን በቂ አይሆንም ይላል ፀሐፊው፡፡ በጠንካራ ዲሲፕሊን መታነፃቸውንም የግድ እንደሚል በመጠቆም፡፡

ስለሆነም በነዚህ ፀሃፊዎች እይታ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል በስራው ግንባር ቀደም መሆን እንዳለበት፣ በአከባቢው ይሁን በሚሰራበት መስሪያ ቤት በጥሩ ዲሲፕሊን የሚታወቅ መሆን እንዳለበት ነው የሚያስረዱን፡፡ይህ ማለት አባሎቹ የድርጅታቸውን ስም በመልካም እንዲጠራ በመልካም ስነ-ምግባራቸውና በአርአያነታቸው በህብረተሰቡ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡

ፓርቲዎች ለቆሙለት ዓላማና የህብረተሰብ ክፍል በዴሞክራሲያዊ አኳሃን በመታገል ከሚያበረክቱት አስተፅኦ ባሻገር አላማቸውን ማራመድ የሚችሉት የዴሞክራሲ ስርዓት ሲገነባ መሆኑን በመገንዘብ የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ፣ የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው የሚያጠያይቅ አይመስለኝም፡፡

በመሆኑም ፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ የሆነ ባህሪይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እነዚሁ ፓርቲዎች አንድ የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ፣ በዚህ የፖለቲካ ዓላማ ለመሰባሰብ የሚፈልጉ ዜጎችን በሙሉ ለማሰባሰብ የሚጥሩና መነሻ መድረሻቸው ዓላማቸው ሊሆን ይገባል፡፡ ዓላማዎቻቸውን ለማራመድ ደግሞ በመጀመርያ እራሳቸው ዓላማዎቻቸውን ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም

ባሻገር ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን በመተንተንና በማቀናበር ለህዝብ የማቅረብ ዓቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን የፖለቲካ አመራር ለመስጠት የማይችል ፓርቲ አንድም የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም፣ አለበለዚያም ተልዕኮውን በአግባቡ ሊወጣ የሚችል አይደለም፡፡

ወደ አገራችን እንመለስና ሰሞኑን የኢህአዴግ ምክር ቤት ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በድርጅትና በመንግስት ከፍተኛ የስልጣን ሃላፊነት ያሉ ነባር አመራሮቹን በአዲሱ ትውልድ የሚተካበት ስርዓት ላይ ውሳኔ እንዳሳለፈ ሰምተናል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች ያቀረቡትን ስልጣን የመልቀቅ ጥያቄም ተቀብሏል፡፡ በመንግስት ስልጣን ላይ ያሉ አመራሮቹን የመተካት ጉዳይንም በተመለከተ፣ ድርጅቱ መጪውን ምርጫ ካሸነፈና ስልጣን ከተረከበ በኋላ የሚከናወን መሆኑንም ይፋ አድርጓል፡፡

ኢህአዴግ አንጋፋውን አመራር ሊተኩ የሚችሉ አባላት አፍርቷል ? ብለን መጠየቁ ትክክልና ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እንደሚታወቀው የኢህአዴግ አባል መሆን የሚፈልግ ሰው በመጀመርያ ደረጃ የፓርቲው ፖሊሲና ስትራተጂ ያመነበት፣ የብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት እስከመገንጠል በማያሻማ አኳሃን የሚቀበልና መሬት በመንግስት ስር መሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ እንደሚሆን ያመነ መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላም አባል ሲመለመል የተማሩ ወጣቶችና ሴቶች፣ በተሰማሩበት ስራዎች ሁሉ ግንባር ቀደም የሆኑ ሰዎችን ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚመለምል ከሰማን ሰነባበተናል፡፡

ይህ የሚያሳየው ኢህአዴግ አባላቱን ሲመለምል የራሱ ፖሊሲና ስትራተጂ በግልፅ አሳውቆ፣ ግለሰቡም የፓረቲውም ህገ-ደምብ ጠንቅቆ ሲያወቅና ከተፅዕኖ ነፃ በሆነበት ሁኔታ ነው፡፡ አምነውበት እንደተቀበሉት ነው፡፡ እሱ ብቻ አይደለም ከመለመላቸው አባላት በስራ ተፈትነው ግንባር ቀደም የሆኑትን በብዛት ወደ ስልጠና በማስገባት አቅማቸው እንዲያጎለብት አድርጓል፡፡ የተለያዩ የአመራር ስልጠናዎችም ሰጥቷል፡፡በዚህ ሂደትም ከተራ አባል ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ደረጃ የበቁ ብዛት ያላቸው ተተኪ አመራሮችን አፍርቷል ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም

ነው ታዋቂው የፖለቲካ ተኝታኝ አሜሪካዊው ራልፍ ናደር “የአመራር ትልቁ ሃላፊነት ብዙ ተተኪ አመራሮችን መፍጠር እንጂ ብዙ ደጋፊዎችን መፍጠር አይደለም” ያለው፡፡

ይህ ማለት ግን ብዙ ደጋፊዎች አያስፈልጉም ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ደጋፊዎች ባፈራህ ቁጥር ከብዙ ውስጥ ብቃት ያላቸውን ተተኪ አመራሮች መውጣት እንደሚችሉ አያጠያይቅም፡፡ ነገር ግን ብዙ አባላቶች አፍርተህ  በብዛት ለአመራር የማታበቃ ከሆነ ፋይዳ አይኖረውም ለማለት ነው፡፡

የገዢው ፓርቲ በዚህ ላብቃና ወደ ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን ደግሞ እንለፍ፡፡ እንደሚታወቀው  የአገራችን ተቃዋሚዎች ግልፅ የሆነ ፖሊሲና ስትራተጂ አላቸው? ብለን ብንጠይቅ ከሞላ ጎደል የሁላችንም መልስ የላቸውም በሚል የምንስማማ ይመስለኛል፡፡

ታድያ! እነዚህ ፓርቲዎች ግልፅ የሆነ ፖሊሲና ስትራተጂ ከሌላቸው እንዴት አባላትን ማፍራት ይችላሉ? በዚህም በዚያም የሚያፈሯቸው አባላትስ ለነገ ተተኪ መሆን የሚችሉ ናቸው ወይ? አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች አባላቸውን የሚመለምሉ በጠራ ፖሊሲና ስትራተጂ ሳይሆን በአደገኛ የኮምዩኒኬሽንና የፕሮፓጋንዳ  ስልት በመጠቀም ነው፡፡ እንዳየነውና እንደሰማነው በተቃዋሚው ጎራ የአባላት ማፍሪያ ዘዴ ጥቅማ ጥቅም፣ ትውውቅና ዝምድና ወዘተ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ መንገድ ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠንካራ አባላት እንዳይሰበስቡ አድርጓቸዋል፡፡ ፡፡ የዚህም ውጤት የሚያመጣው ያለውን ጣጣ ደግሞ በተቃዋሚዎች ጎራ ጎልቶ እየታየ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ መሪዎች እርስ በርሳቸው ሲሰዳደቡና አንዱ የአንዱን ክብርና ሰብእና ሲያጎድፉ ነው የሚታዩት፡፡ ይህ የሚያሳየን ደግሞ የጠራ ፖሊሲና ስትራተጂ ባለመኖሩ መሪዎቹ ራሳቸው በመርህ ሊገዙ አለመቻላቸው ነው

በግልፅ የሚያሳየው፡፡ስነ-ምግባር የጎደለው የፓርቲ መሪ በየትኛው ስሌት ነው ጥሩ አባላትን ሊያሰባስብ የሚችለው?

"የመሪ እንጂ የተመሪ ሰነፍ የለም " እንደሚባለው የተቃዋሚ መሪዎቹ የጠራ ፖሊሲ ባለመያዛቸውና የሚያሰባስቧቸው አባላትም ምክንያታዊ በሆነ አካሄድ ባለመሆኑ የመሪዎቹ ስንፍና ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል፡፡

ያሰባሰቧቸውንም አባላት በተለያዩ ስልጠናዎች አቅማቸውን ማጠናከር ሲገባቸውና ለነገ ተተኪ የሚሆኑ መሪዎችን ለማፍራት ጥረት ለማድረግ ማቀዱ በአብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የማይታሰብ ነው፡፡ ከላይ የጠቀስኩትን ፀሐፊ እንደሚያትተው "አንድ ፓርቲ ጠንካራ ነው ተብሎ የሚፈረጀው ያሉትን አባላት ለተለያዩ የአመራር እርከኖች የሚያበቃ ሲሆን ነው"፡፡ አብዛኛዎቹ የኛ አገር ተቃዋሚዎች ግን የግለሰብ የበላይነት የሚታዩባቸውና "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ዓይነት አካሄድን የሚከተሉ በመሆናቸው ፓርቲያቸውን ተቋማዊ ይዘት እንዳይኖረው አድርገዋል፡፡

ባለፈው የስልጣን መተካካትን አስመልክቶ በኢህአዴግ በኩል የተላለፈውን ውሳኔ ምክንያት በማድረግ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ኢህአዴግ በመተካካቱ ላይ ያስተላለፈውን ውሳኔ ሲተቹት ተስተውሏል፡፡ የገዢው ፓርቲ ጠንካራ ጎን ምንድነው? እኛስ ከዚህ ምን ዓይነት ትምህርት እንወስዳለን ብለው ጠንካራ ተቋም ከመፍጠር ይልቅ፣ የራሳቸውን ጓዳ ሳይሸፍኑ የሚያስተምር እርምጃ የወሰደውን ፓርቲ ወደ መተቸት መሯሯጣቸው ለትዝብት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል፡፡

የቀድሞ ቅንጅትና አሁን የመኢአድ ሊቀመንበር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል፣ የኢህአዴግ የመተካካት ስራ "አርቲፊሻል" በማለት ሲተቹት ሰምተናል፡፡ የፓርቲው መሪ ከላይ እንደተገለፀው ያሏቸውን አባሎች ወደ መሪነት ሊያበቋቸው ባለመቻላቸው እኔ ያላደረግኩት እንዴት ሌሎች ፓርቲዎች ሊያደርጉት ይችላሉ

በሚል ከልክ ያለፈ የትምክህተኝነት ስሜት የኢህአዴግን የአመራር የመተካካት ሂደት ሊደረግ የማይችል እንደሆነ ሊያስረዱን ሞክረዋል፡፡

በሌላም ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከስልጣን የመልቀቅ ውሳኔ አስተያየት ሲሰጡ “በህቡዕ ስልጣናቸውን ይዘው ይቆያሉ” ብለውናል፡፡ እንግዲህ የአገራችን የተቃዋሚ መሪዎች ምክንያታዊ ባልሆነ አነጋገርና ህዝቡስ ምን ይለናል ሳይሉ በስሜት መነዳትን ቀጥለዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ለአገራችን ብሎም ለመላው ህዝባችን መጪው ተስፋ ካለማሰብ የመነጨና ግለሰባዊ አመለካከታቸውን የሚያጎላ መሆኑን ሳይገነዘቡ ያልፉሉ ብዬ አልገምትም፡፡ ለነገሩ “አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት እይሰማም” ይባል የለ!

ሲጠቃለል አንድ አገር የዴሞክራሲያዊ ብዙህነትን ስታሰተናግድ ከሱ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ተቋማትና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማስተናገዷ የግድ ነው፡፡ ዴሞክራሲ ስር እንዲሰድ ደግሞ ፓርቲዎቹ ተቋማዊ የሆነ ይዘት ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም፡፡ አንድ ፓርቲ ተቋሚዊ ይዘት አለው ሊባል የሚችለው ደግሞ ያለውን ራእይ ብስለት ባለውና በጠራ ፖሊሲ ላይ የሚንዝ ከሆነና ያለውን አባልም የጠራ አስተሳሰብ ማስያዝ የሚችል ከሆነ ነው፡፡ አለበለዚያ በቀላሉ የሚተን (volatile) ነው የሚሆነው፡፡

የአገራችን ተቃዋሚዎችም ተቋሚዊ ይዘት እንዲኖራቸውና ተጨባጭ የሆነ መርህ ይዘው የሚያፈሩትን አባል የነገ አመራር ሊሆን ስለሚችል ብቃትና ክህሎት የሚያስጨብጥ ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ የአሁኑ አካሄዳቸው ግን ተቋማዊ ይዘት የሌለውና አባላትን በጥቅማጥቅም በማሰባሰብ ላይ ያተኮረ ስለሆነ በቀላሉ ሊተኑበት የሚችሉ አጋጣሚዎች አሉ፡፡

ለነገሩ የአገራችን ተቃዋሚዎች በተለይ ከምርጫ`97 በኋላ አንዴ ይሰባሰቡና እንደገና ይበታተናሉ፣ አንዳንዴማ መቼ እንደተሰባሰቡ ሳንሰማ እንደተበታተኑ (እንደተነኑ) የምንሰማበት አጋጣሚ አለ፡፡ ይህ ደግሞ ለአገራችንም

ለህዝባችንም ጥሩ የሆነ አካሄድ ስላልሆነ አካሄዳቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል እላለሁ፡፡

ገዢው ፓርቲ በመተካካቱ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔና ቀድሞ አባሎችን በማብቃት ዙርያ ላይ ያደረገውን ዝግጅት ሊመሰገን የሚገባና ከኛም አልፎ ለአህጉራችንም ትልቅ ትምህርት ይሆናል ብየ አስባለሁ፡፡ሰላም!